የአማራ ኅብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ | Amhara Heritage Society of Minnesota
1861 University Ave W, St. Paul, MN 55104 Suit S-340
Ph: 763-291-2501 email: amharaMN@gmail.com www.amharaMN.org

September 30, 2019 Ref. # 00011

ለአቶ ደበበ አበራ ሳከሎ, የዲያስፖራ ጉዳዮች አማካሪ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሊፐብሊክ ቆንስላ ጄኔራል ጽ/ቤት
2550 University Ave. W Suite 314N
Saint Paul, MN 55114

ጉዳዩ : - በሴፕቴምበር 29/2019 በሚደረገው የእራት ግብዣ ላይ ስላለመገኘት

ውድ የተከበሩ አቶ ደበበ፡-

ሴፕቴምበር 09/23/2019 ዓ/ም በጻፉልን ደብዳቤ የቆንጽላ ጽህፈት ቤቱ የዘመን መለወጫን ምክንያት በማድረግ በሚያደርገው የእራት ግብዣ ላይ እንድንገኝ ስለጋበዙን ምስጋና እናቀርባለን።

ነገር ግን በአሁኑ ወቅት በአገራችን በኢትዮጵያ በአማራው ወገናችን እና የኢትዮጵያ ባለውለታ በሆነችው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ እየደረሰ ባለው ጥቃት ላይ እና በሰፈነው ስርዓት አልበኝነት ላይ የመንግስት ምላሽ አመርቂ ባለመሆኑ እና እዚህም ባለንበት በሚኔሶታ ግዛት ቆንጽላ ጽህፈት ቤቱ በብሔረሰቦች ድርጅቶች መካከል በሚያሳየው መድሎአዊ አሰራር እና የአማራውን ድርጅት ገሸሽ የማድረግ ሁኔታ ላይ ባለን ቅሬታ የተነሳ በእራት ግብዣው ላይ መገኘቱን ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም።

ይህ ውሳኔያችን የጸደቀው የተሳታፊዎችን ስም ካስተላለፍንላችሁ በኋላ ከአጠቃላይ አባሎቻችን ጋር በተደረገ ውይይት በተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ እና እኛም የአባሎቻችንን ውሳኔ መከተሉ ግድ ስለሆነብን በግብዣው መገኘት አልቻልንም። በዚህ በመጨረሻ ደቂቃ በተሰጠ ውሳኔ ምክንያት ከግብዣው በፊት ቀድመን አለመምጣታችንን ለማሳወቅ ባለመቻላችን ይቅርታ እየጠየቅን በቅርቡ ከርስዎ ጋር ተገናኝተን በቅሬታዎቻችን ላይ ተወያይተን እና መፍትሄ ፈልገን ወደፊት በመግባባት አብረን እንደምንሰራ ተስፋ አለን።

የሚመችዎትን ቀን እና ሰዓት ቢገልጹልን ቢሮዎት መጥተን ወይንም ቦታ አመቻችተን በእያንዳንዱ ቅሬታዎቻችን ላይ ውይይት ለማድረግ እና መፍትሄ ለመተለም ምኞታችን ነው። ይህ የቆንጽላ ጽህፈት ቤቱም ፍላጎት እንደሚሆን እንገምታለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!

ከሰላምታ ጋር

የዚህዓለም መስፍን - ሊቀመንበር

ግክባጭ፡-

ለኢትዮጵያ ኤምባሲ - ዋሺንግተን ዲሲ , ዩኤስ አሜሪካ

ለኢትዮጵያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር - አዲስ አበባ , ኢትዮጵያ

ለአማራ ክልላዊ መንግስት - ባህር ዳር , ኢትዮጵያ